የ2013 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የ1ኛው ሩብ ዓመት የሒሳብ ትምህርት የመጀመሪያ ማስታወሻ ለ5ኛ ክፍል

ምዕራፍ አንድ

ሙሉ ቁጥሮችና አራቱ መሰረታዊ ስሌቶች

1.1. ከ1,000,000የሚበልጡሙሉቁጥሮች

1.1.1. እስከ1,000,000ያሉሙሉቁጥሮች

☐0 ፣ 1 ፣ 2 ፣ 3 ፣ 4 .... ሙሉ ቁጥሮች ይባላሉ፡፡

☐1 ፣ 2 ፣ 3 ፣ 4 ..... የመቁጠሪያ ቁጥሮች ይባላሉ፡፡

☐በሙሉ ቁጥሮች የቁጥር ስርዓት ውስጥ አስር መሰረታዊ የቁጥር ሆሄያት አሉ፡፡ እነዚህም

0 ፣ 1 ፣ 2 ፣ 3 ፣ 4 ፣ 5 ፣ 6 ፣ 7 ፣ 8 እና 9 ናቸው፡፡

☐እነዚህን የቁጥር ሆሄያት በመጠቀም ማንኛውንም ሙሉ ቁጥር መግለፅ ይቻላል፡፡

☐በአንድ ሙሉ ቁጥር ውስጥ የሚገኙ መሰረታዊ የቁጥር ሆሄያት የቤት ዋጋ አላቸው፡፡ እነርሱም

የሚሊዮን ቤት	የመቶ ሺ ቤት	የአስር ሺ ቤት	የሺ ቤት	የመቶ ቤት	የአስር ቤት	የአንድ ቤት
↓	↓	↓	↓	↓	↓	↓
1,000,000	100, 000	10,000	1,000	100	10	1

ምሳሌ 7,891,432

2 አንዶች 3 አስሮች 4መቶዎች 1 ሺዎች 9አስር ሺዎች

8መቶ ሺዎች

7ሚሊዮኖች

ምሳሌ 682,475 ን በአስር ብዜቶች ተተንትኖ ሲገለፅ

682,475 = (6X100,000)+ (8X10,000)+ (2 X1000)+ (4X100)+ (7X10)+ (5X1)

መልመጃ

ከሚከተሉት ቁጥሮች ውስጥ የ6 ቁጥርን የቤት ዋጋ ግለፁ፡፡

ሀ. 4,761 _____

ለ. 406,117 _____

ሐ. 18,416 _____

መ. 163,514 _____

ሠ. 258,629 _____

1.1.1. ከ1, 000,000 የሚበልጡ ሙሉ ቁጥሮች

□አንድ ሚሊዮን ባለ ሰባት ሆሄ የሆነ ቁጥር ነው፡፡

አንድ ሚሊዮን 10 መቶ ሺዎችን ወይም 1,000 ሺዎችን (1000 x 1000)ይወክላል፡፡

ምሳሌ1.ሙሉ ቁጥርን በአሀዝ መፃፍ

ሶስት ሚሊዮን አራት መቶ ሰባ ሺህ ሃምሳን በአሃዝ ፃፉ፡፡

ሶስት ሚሊዮን ⟶ 3,000,000

አራት መቶ ሺህ ⟶ 400,000

ሰባ ሺህ ⟶ 70,000

ሀምሳ ⟶ 50

= 3,470,050

ቀዳማይ እና ተከታይ

ለማንኛውም ከዜሮ ለተለየ ሙሉ ቁጥር “ወ”

ቀዳማይ ወ -1 ሲሆን

ተከታይ ወ +1 ይሆናል::

ምሳሌ፡- ሀ. ከ3,465,287 በፊት ቀድሞ የሚመጣው ሙሉ ቁጥር ስንት ነው?

ከ3,465,287 በፊት ቀድሞ የሚመጣው ሙሉ ቁጥር ከዚህ ቁጥር በአንድ እንደሚያንስ አስታውሱ፡፡ ስለዚህ የ3,465,287 ቀዳማ ይ 3,465,286 ነው፡፡

ለ. የ 2,746,352 ተከታይ ሙሉ ቁጥር ስንት ነው? ከዚህ ቁጥር በአንድ የሚበልጥ ቁጥር ተከታይ ነው፡፡

ስለዚህ የ 2,746,352 ተከታ ይ 2,746,353 ነው::

መ ል መ ጃ

1. ለሚከተለውን ቁጥር ቀዳማይና ተከታይ ፃፉ፡፡

   ሀ. _____ 3,406,705_____

2. ሙሉ ቁጥሩን በፊደል ፃፉ፡፡

   ሀ. 1,532,489_____

3. የሚከተለውን ቁጥር በአሃዝ ፃፉ፡፡

   ሀ. አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ አራት ሺህ ሃያ _____